# መ ቅ ድ ም

ይህ ሃያ ዘጠነኛዉ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት እንዳለፉት ተመሣሣይ እትሞች ሁሉ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ ቀርቧል:: መጽሔቱ ስለ አገሪቱ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚገለፁ ልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የያዘ ስለሆነ ለፖሊሲና ለልማት ፕሮግራሞች ዝግጅትና ግምገማ ብሎም ለምርምር ተግባሮች በመነሻነት እንደሚያገለግል ይታመናል::

በተከታታይ ዘመናት የሚታቀዱትን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ዘመን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕቅዶች ለማዘጋጀትና የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን በአገራችን ለመተግበር ትክክለኛና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን መሰብሰብና ሥርዓት ባለዉ መንገድ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ የወቅቱ ተቀዳሚ ተግባር ነዉ:: የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በማያሰልስ ሁኔታ ጥራቱን በማሻሻልና ወቅታዊነቱን በመጠበቅ ተፈላጊ የሆኑ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማቅረብ ጠቅላላ ቆጠራዎችና በርካታ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ናሙና ጥናቶችን ያካሄደ ሲሆን፣ አሁንም በማካሄድ ላይ ይገኛል:: በሌላ በኩል የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል በተለይም ይህን መጽሔት ወቅቱን ጠብቆ እንዲታተም ከሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከመንግሥት ድርጅቶች፣ ከሕዝባዊ ድርጅቶችና ከግለሰቦች ጭምር ከፍተኛ ትብብር ማግኘት አስፈላጊ ይሆናል:: በመሆኑም እያደገ የመጣዉን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎትና ጥያቄ ለማሟላት እንዲቻል የሚመለከታቸዉ ሁሉ ጥያቄው ሲቀርብላቸው ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በወቅቱ በማቅረብ በኩል ከምንግዜዉም የበለጠ ትብብር እንዲያደርጉ የባለሥልጣኑ መ/ቤት በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ ይወዳል::

የአገሪቱን ማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በበለጠ በመረዳት በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ የልማት ዕቅዶችን ለመቀየስና ለመገምገም እንዲቻል የባለሥልጣኑ መ/ቤት በተለይ ከ1972 ጀምሮ በርካታ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የሥነ-ሕዝብ ሁኔታዎችን የሚያንፀባርቁ መረጃዎች ለመሰብሰብ ጥናቶችን ሲያካሄድ የቆየ ሲሆን ከነዚህም መካከል የግብርና፣ የዋጋ፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ፣ የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ደህንነት፣ የመካከለኛና የትላልቅ ማምረቻ እና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪዎች እና፣ የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የጎጆ/ዕደ ጥበባት ኢንዱስትሪዎች፣ መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ፣ የአከፋፋይና የአገልግሎት ሰጪ ንግድ፣ የሰዉ ኃይል፣ የሥነ-ሕዝብ፣ የቤተሰብና የወሊድ ሁኔታ፣ የጤናና የአመጋገብ፣ የሥነ-ሕዝብና የጤና፣ የሕፃናት የሥራ ስምሪት ሁኔታ፣ የተከታታይ የሥራ ስምሪት ሁኔታ፣ ... ወዘተ ጥናቶች ይገኙበታል::

ከላይ ከቀረቡት ናሙና ጥናቶች በተጨማሪ የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በግንቦት ወር 1976 እና ሁለተኛውን ደግሞ ከጥቅምት 1 ቀን 1987 ጀምሮ በማካሄድና በቆጠራዉ የተሰበሰቡትን መረጃዎች የማቀነባበር፣ የመተንተንና የሪፖርት ዝግጅት ተግባራት ተጠናቀው ከቆጠራው የተገኙ ውጤቶችና የሚያቀርቡ በርካታ ሪፖርቶች ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የግብርና ናሙና ቆጠራ በ1994 ዓ.ም. ተከናውኖ ውጤቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በወቅቱ ተሰራጭቷል:: በአሁኑ ወቅትም ለሦስተኛ ጊዜ በ1999 ዓ.ም. የሚካሄደውን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ለማከናወን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በተለይም የቆጠራ ካርታ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል::

የባለሥልጣን መ/ቤቱ በየሴክተሩ ከሚያከናውናቸው መደበኛ የኢኮኖሚ ጥናቶች በተጨማሪ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከምንጊዜውም በበለጠ ወቅታዊ የኢኮኖሚ ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለማመንጨት የሚያስችሉ ጥናቶችን ለማከናወን አቅዶ በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው:: ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን አቅርቦት ለማሻሻል የባለሥልጣን መ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት በፌዴራልና በክልል የሚገኙ መንግሥታዊ ድርጅቶችን የስታቲስቲክስ መዛግብት አያያዝ፣ ስታንዳርድና ምደባ በማጥናት የመረጃ ፍሰት የሚሻሻልበትን ሁኔታ በመቀየስ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ሥርዓት በመወሰን ትርጉምና ምደባ በቅርቡ እንደሚያወጣ ይጠበቃል::

ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለማጠናቀርና በተለይም ስርጭቱን ለማቀላጠፍ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን አጠቃቀምን ተግባራዊ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በማከናወን ላይ ናቸው::

በመጨረሻም ለመጽሔቱ ዝግጅት የሚያስፈልጉትን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በማቅረብ ረገድ የተባበሩንን የመንግሥት መ/ቤቶች፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም ለመጽሔቱ ዝግጅት አስተዋጽኦ ያበረከቱትን የመ/ቤቱን ባልደረቦች ሁሉ በዚህ አጋጣሚ ለማመስገን እወዳለሁ::

ሣሚያ ዘካሪያ
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
ተ/ዋና ሥራ አስኪያጅ

# FOREWORD

The twenty-ninth issue of the Statistical Abstract, as in the past is prepared in Amharic and English languages. The Publication presents a wide range of data illustrating various socio-economic conditions of the country. The statistical information contained in the publication provides basic information for policy and programme formulation, evaluation and as input for under taking socio - economic activities.

Reliable and timely statistical data are required for the purpose of launching the short, medium and long-term socio-economic development plans and for realizing the free market economy system that is in operation. Hence, the collection of reliable and timely data and the analysis and presentation of the same are the main task of current statistical development. In this respect, the Central Statistical Authority has made significant progress in furnishing the required statistical data by undertaking population and housing censuses and several socio-economic and demographic surveys.

On the other hand, the timely publication of the Statistical Abstract, the Central Statistical Authority can discharge its responsibility only if it obtains the active and timely participation of the concerned ministries, government agencies, mass organizations as well as individuals who provide the basic inputs to this publication. Hence, the office urges all those concerned to enlist further cooperation for the timely publication of the Statistical Abstract.

In the 1980's the Authority carried-out several socio-economic and demographic surveys in the country and these surveys include Agricultural; Price; Household Income; Consumption and Expenditure; Welfare Monitoring; large and Medium Scale Manufacturing and Electricity Industries; Small Scale Manufacturing Industries; Cottage/Handicraft Manufacturing Industries; Informal Sector; Distributive Trade and Services; Manpower; Family and Fertility; Health and Nutrition; Demographic and Health; Child Labour; Current Employment Unemployment,.... etc.

Furthermore, the first and the second National Population and Housing Censuses were conducted in May 1984 and in October 1994, respectively. The data processing, analysis and preparation of the reports have been completed and the numerous reports that present the results of the census have been disseminated to the users. Similarly, the first ever Ethiopian Agricultural Sample Enumeration was conducted in 2001/2002 and the census data have been processed, evaluated, analyzed and the agricultural census reports have been prepared at woreda, zonal, regional and country levels and disseminated to data users. At the moment, the preparatory activities including census cartographic map works are under way to conduct the third Population and Housing Census in 2007 as per schedule.

The Authority has also given prior attention to the current business surveys in addition to its regular sample and census activities. To implement this a detailed survey action plan has been prepared and the actual data collection activities in the sectors are under way.

In order to improve the existing administrative data flow in the country, the Authority has carried-out a study in some Federal and Regional institutions and collected information on statistical record systems, standards, concepts and definitions used ...etc. Based on this study the Authority is expected to prescribe a system for collection, compilation, classification and flow of statistical data. Currently, the Authority's top priority is strengthening its data dissemination strategy and enhancing its capacity in utilizing the information communication technology for the statistical development.

In conclusion, compliments are due to the various government ministries, agencies, mass organizations and individuals for their cooperation in providing the required data for the preparation of this Statistical Abstract as well as to the staff of the Central Statistical Authority for their efforts in producing this edition.

Samia Zekaria
Acting General Manager
Central Statistical Authority